# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 309 ሚያዝያ 3 2006


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ህወሓት ከሥልጣን መወገድ ይኖርበታል ብሎ ያምናል። ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ መገለል፣ መረገጥ፣ መጋዝ፣ መሰደድ፣ መደብደብ፣ የማይቀርልን በመሆኑ ሥቃያችንን ለመቀነስ ወያኔን ማስወገድ ይኖርብናል ብሎ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ መንገዶችና ምክንያቶች የምናደርጋቸው ትግሎች ወደ አንድ አቅጣጫ ያመራሉ ብሎ ያምናል። ትግሎቻችን ዞሮ ዞሮ ህወሓትን ከሥልጣን ወደ ማስወገድ ማምራታቸው ግልጽ ስለሆነ ለዚህ የሚያስፈልገውን ስነልቦናዊና ቁሳዊ ዝግጅቶችን እናድርግ ይላል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ኢትዮጵያ ዉስጥ የሰብአዊ መብት አያያዝ በከፍተኛ ሁኔታ እየዘቀጠ ነዉ

ለኢትዮጵያው ፋሽስታዊ አገዛዝ እጅግ ከፍተኛውን የእውቀት፣ የአይነትና የገንዘብ እገዛ በማድረግ የሚታወቀው የአውሮፓ ሕብረት ፓርላማ አገዛዙ በሀገሪቱ እጅግ የገዘፈ የሰብአዊ መብት ረገጣ ያሰፈነ መሆኑን ምስክሮችን አስቀርቦ በማዳመጥና የአባላቱን የግል ትዝብት በመጨመር ከፍተኛ ትችት መሰንዘሩ ተሰማ።

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙትን የማእከላዊና ቃሊቲ ወህኒ ቤቶችን ጨምሮ በኦጋዴንና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች አገዛዙ እያደረሰው ያለውን አፈና፣ ግርፋት፣ ያለምክንያት ማሰር፣ ግድያና አስገድዶ መድፈር ምስክርነት በዝርዝር ያደመጠው የአውሮፓ ሕብረት ፓርላማ በገፍ እያፈሰስን ያለነው አመታዊ የገንዘብ እገዛም በትክክለኛው መንገድ እየዋለ ካለመሆኑም በተጨማሪ ለሙስና የተጋለጠ ነው በማለት አስረግጦ ተወያይቷል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛውን የሰብአዊና የልማት ርዳታ ከሚወስዱት ሀገራት ቀዳሚዋ መሆኗን በአንክሮ የገለጸው ይህ የአወሮፓ ሕብረት ፓርላማ ውይይት፤ ይህ ሁሉ እገዛ ያላግባብ በዘፈቀደ ሲውል፣ ለሙስና ሲጋለጥና ከዚያም በላይ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ለአገዛዙ የፖለቲካ ፍጀታ ለፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ማሰባሰቢያነት እንዲሁም ተቃዋሚዎችን ለማጥቂያነት ሲውል በአዲስ አበባ የሚገኙ የምራባዊያ ሀገሮች ዓለማቀፍ ተቋማትም ሆኑ ኤምባሲዎቻቸው ምንም አለማለታቸውና ነገሩን እንደቀላል መተዋቸው በጣም አሳፋሪ ነው ይህ ደግሞ ከአውሮፓ ሕብረት ህግና መመሪያ ተቃራኒ ነው ሲል አማሯል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የ2007ቱ ምርጫ በተቃረበ ቁጥር የወያኔ አፈና፤ እስርና እንግልት እየጨመረ መሆኑ ተነገረ

በትጥቅ ትግል እንፋለመዋለን የሚሉትን ሀገር ወዳድ ሃይሎች ሁሉ በታዛዥ ባርለማው "ሽብርተኞች" ያለውና በሀገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን የሚሉትንም "እንዳለመታደል ሆኖ ጠንካራ ተቃዋሚ የሉንም" ሲል የነበረው ሕወሃት መራሹ ወያኔ በ2007 ዓ/ም ይደረጋል ተብሎ ከሚጠበቀው ሀገራዊ ምርጫ እጅግ ቀድሞ እየታየ ያለውን የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎችን የተደራጀና ጠንካራ እንቅስቃሴ መቋቋም ባለመቻሉ ወደ አፈናና እስራት እየተሸጋገረ መሆኑ ታወቀ።

በተቃዋሚው በኩል የተጠየቁ ሰላማዊ ሰፎችን ከመከልከል ጀምሮ የተፈቀዱትንም በተለያዩ መንገዶች እስከማደናቀፍ የደረሰውና በነጻ ውድድር የማያምነው ፋሽስት ወያኔ ሰልፈኞችን ማዋከብን ጨምሮ በመደብደብና በእስራት እያንገላታ መሆኑን ተጎጅዎች አጋለጡ።

በአዲስ አበባና በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ያለው የተቃዋሚዎች ከፍተኛ እንቅስቃሴ አልጋ ባልጋ እንዳልነበር የሚጠቅሱት አንዳንድ ታዛቢዎች ሆኖም ግን አሁን ሕወሃት መራሹ ጉጅሌ እየወሰደው ያለው እርምጃ ተስፋ የመቁረጥ ይመስላል ይላሉ።

ከዚህ በፊት ተቃዋሚዎች ሰልፍ ወይም ስብሰባ ሲጠሩ ሕወሃትም በጎን ሌላ ዝግጅት በማዘጋጀት ባልመጡት ላይ ከፍተኛ ቅጣት በመጣል ያስፈራራ እንደነበር ያስታወሱት ታዛቢ በዚህ መንገድም አልሳካ ያለው ይህ አገዛዝ ወደ ስብሰባም ሆነ ወደ ሰልፍ መውጫ ቦታዎችን በወታደር በማዘጋት ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዳይኖር በማድረግ ለማደናቀፍ ሙከራ አድርጓል ብለዋል። ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ባለመሳካቱ የተነሳ ሰዎች እየተመረጡና እየተጠኑ ወደ እስር ቤት

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ሲራጅ ፈርጌሳ በአንድ ዘር ቁጥጥር ስር የሚገኘዉን ሰራዊት የብሔር ተዋጽኦ አደነቀ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ያረቀቀው የይስሙላ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 87 የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን አገዛዙ ላለፉት 19 ዓመታት ራሱ ህዝብን በማጭበርበር ረጅም እድሜ ለመግዛት ይረዳው ዘንድ ያረቀቀውን የህገ መንግስቱን አንቀጽ በመጣስ በተለይም በመከላከያው አመራር ላይ የአንድ ብሄር የበላይነት በማስፈን ስልጣኑን ለማስጠበቅ እየሰራ መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉጅሌው ወያኔ የመከላከያ ሚኒስተር ተብየ ሲራጅ ፈጌሳ ለወያኔው አሻንጉሊቱ ፓርላማ የ2006ን ሪፖርት ዋቢ በማድረግ የሠራዊቱ የብሔር ተዋጽኦ እየተመጣጠነ መምጣቱን በመደስኮር ለማስረጃነትም ከአጠቃላይ የመከላከያ ሠራዊቱ አባላት የአማራ ብሔር ተዋጽኦ 29.46 በመቶ በመሆን በቀዳሚነት እየመራ ይገኛል ሲል የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተዋጽኦ 25.05 በመቶ በመሆን በሁለተኛ ደረጃ፤ የኦሮሞ ብሔር 24.45 በመቶ የሦስተኛ ደረጃን ይዟል፤ የትግራይ ብሔር ተዋጽኦ ወደ 17.47 በመቶ በመውረድ በአራተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ሲል ዳግም ህዝብን ለማደናገርና ለአገዛዙ እንዲመች ተደርጎ በውሸት የተቀሸረ የቅጥፈት ሪፖርቱን አሰምቷል።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በመከላከያ ሰራዊቱ የአመራሩ ክፍል የብሄር ተዋጽኦ እስካልተመጣጠነ ድረስ ታች ባለው የሰራዊት አባል የቁጥር ጋጋታ ብቻ «ተዋጽኦውን አሟልተናል» ብሎ መደስኮር ዳግም አገዛዙ ለህዝብ ያለውን ንቀት ከማሳየቱ ውጭ ሌላ ምንም ትርጉም አይሰጥም። የመከላከያ ሰራዊቱ አመራር በአንድ ብሄር የተሞላና የብሄር ተዋጽኦን በማማከል የተገነባ አለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የዛሬ ሁለት አመት ግንቦት ሰባት በኢትዮጵያ መላከያ ሰራዊት ዉስጥ የተዘረጋዉን የወያኔ የዘረኝነት መረብ አደረጃጀት በመረጃ በማስደገፍ ለህዝብ ማቅረቡ ይታወሳል። ግንቦት ሰባት በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ያለውን የወያኔን ዘረኝነት የሚያጋልጡ መረጃዎችን ከራሱ ከወያኔ ጓዳ እየፈለፈለ አዉጥቶ ለህዝብ የሚያቀርበዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን ዘረኝነት አያውቀዉም በሚል አስተሳሰብ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በየቀኑ ደሙን እንደ መዥገር የሚመጠዉን ወያኔን የመሰለ የጀርባ ላይ አጥንት ተሸክሞ መኖር የለበትም ብለን ስለምናምንና እንደዚህ ህዝብ በገዛ አገሩ "እኩል አደረግንህ" ብለዉ በሚነግሩት ከሀዲዎች ቅኝ አገዛዝ እየተገዛ መሆኑን ደግመን ደጋግመን ለማሳወቅ ነዉ።

## ፋሽስቱ ወያኔ በንጹሃን ዜጎች ላይየሚያደርሰውን በደል በተጠናከረ ሁኒታ መቀጠሉ ተሰማ

በወልድያ ከተማ ከ50 በላይ የሚሆኑ ግለሰቦች የሚኖሩበት ቤት በኢንቨስትመንት ስም ለአገዛዙ ቅርበት አለው ለተባለ ባለሀብት መሰጠቱን ተከትሎ በ 24 ሰዓት ውስጥ ቤታችሁን ለቃችሁ ውጡ መባላቸውን በመቃወማቸው የወያኔ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች ግለሰቦችን ማሰራቸው ተሰማ። የከተማው ከንቲባ ፀሐዩ መንገሻ፣ የዞን ብአደን ሀላፊ አበባው ሲሳይ እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገዛዙ አገልጋይ ካድሬዎች ሲጠየቁ ይህ ጉዳይ ከአቅማችን በላይ ስለሆነ አይመለከተንም ማለታቸው ህብረተሰቡን ማስቆጣቱ ተዘግቧል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሶማሌ ክልል ረር ባሬ ዉስጥ በተቀሰቀሰ ግጭት 16 ሰዎች መታሰራቸውን የአገር ውስጥ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ።ከአስተዳደር ጋር በተያያዘ ያነሱዋቸውን ጥያቄዎች ተከትሎ ከፋሽስቱ የወያኔ አገዛዙ ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ የሆኑት የሶማሌ ክልል የየረር ጎሳ አባላት ውስጥ16 ሰዎች መታሰራቸው ታውቋል።

ከወራት በፊት በፋሽስቱ ወያኔ በተሾሙ የክልሉ ቱባ ባለስልጣናት ትእዛዝ በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው ልዩ ሚሊሺያ እየተባለ የሚጠራው ሃይል በጎሳው አባላት ላይ በከፈቱት ጥቃት ከ50 ያላነሱ ሰዎች መገደላቸውን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ድርጊቱ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድላቸው ለፋሽስት ወያኔ አሻንጉሊት ሃይለማርያም ደሳለኝ ለማሳወቅ ወደ አዲስ አበባ የሄዱ 19 የአገር ሽማግሌዎች ካለፉት 2 ወራት ጀምሮ የታሰሩ ሲሆን እስካሁን አልተፈቱም። ከ60 እስከ 85 እድሜ ያላቸው የአገር ሽማግሌዎች ህክምና ሳይቀር ተነፍገው ከእስር ቤት እስር ቤት እየተዘዋወሩ እንዲታሰሩ በመደረጉ ህዝብ ለመጠየቅ እንደተቸገረ ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

## በኢትዮጵያ የመብቶች ትግሎች ሁሉ ህወሓትን ከሥልጣን ወደ ማስወገድ አቅጣጫ ያመራሉ!!!

የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ መሪዎች የክስ ሂደት በበርካታ አሳዛኝ ጉዳዮች የታጀቡ ቢሆኑም የሚሰጡት ትምህርት ግን ከፍተኛ ነው። እነዚህ ወገኖቻችን "ችሎት" በተሰኘው የአገዛዙ የድራማ መድረግ በመገኘት ፍትህን ለመግደል ካባ ለብሰው "ዳኞች" ተብለው ለተኮፈሱ የአገዛዙ ተላላኪ ካድሬዎች እና ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጓቸው ጠንከር ያሉ ንግግሮች ካድሬ "ዳኞችን" አሳፍረዋል፤ ኢትዮጵያዊያንን ግን አኩርተዋል። እኚህ ወገኖቻችን ከወያኔ ችሎት ፍትህ ይገኛል የሚል ብዥታ ባይኖራቸውም መድረኩን መልዕክት ለማስተላለፊያነት ተጠቅመውበታል። በዚሁ መድረክ በአገዛዙ እጅ ከወደቁበት ጊዜ ጀምሮ እየደረባቸው ስላለው ሰቆቃ ሲናገሩ አድማጮች ሊቆጣጥሩት የማይችሉት ሐዘንና እልህ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

ወያኔ እንዲህ ዓይነቱ ጭካኔ የሚፈጽመው በሙስሊም መሪዎች ላይ ብቻ አይደለም። የህግ እውቅና የተሰጣቸው መብቶቻቸው እንዲከበርላቸው በጠየቁ ወገኖቻችን ሁሉ ተመሳሳይ ሰቆቃ ሲፈጸም ኖሯል፤ አሁን እየተፈጸመ ነው። "ኑሮ ከበደን" ያሉ ወጣቶች ተደብድበዋል። "የእርሻ መሬት አጣን" ያሉ ገበሬዎች ከያዙት ቁራሽ መሬት ተፈናቅለዋል፣ ተግዘዋል፣ ከነልጆቻቸው ለጎዳና ኑሮ ተዳርገዋል። በሀረር እና በአዲስ አበባ ከተሞች እንደታየው "ነግደን እንኑር" ባሉ ነጋዴዎች ላይ ከአቅም በላይ ከሆነ ግብር ጀምሮ በንብረታቸው ላይ እሳት እስከመልቀቅ የደረሰ አረመኔዓዊ ድርጊት ተፈጽሟል።

በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 18 መሠረት እያንዳንዱ ሰው በግሉም ሆነ በጋራ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተልና የማስተማር፤ ያልፈለገውን ደግሞ የመተው መብት አለው። ስለሆነም የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ተግባራት በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እውቅና ለተሰጣቸው መብቶቻቸው መከበር ያደረጉት ትግል ነው። ለወጉ ያህል "ሕገ መንግሥት" ተብሎ በሚጠራው ኢትዮጵያዊያንን ለመክሰሻነት ብቻ በሥራ ላይ በሚወለው ሰነድ ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም ዓለምዓቀፍ እውቅና ያገኙ መብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ተረግጠዋል። ለእነዚህ መብቶች መከበር በጽናት የቆሙ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች ከተራ የመንደር ካድሬና ጆሮ ጠቢ እስከ እስከ ከፍተኛው እርከን ባለ ባለሥልጣኖች ተዋክበዋል፤ ሰቆቃ ተፈጽሞባቸዋል።

ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለእምነት መብቶቹ መከበር እስካሁን ያደረገው ተጋድሎ የሚደነቅ ነው። የተቀናጁ እንቅስቃሴዎቹ፣ ተምሳሌታዊ የተቃውሞ ምልክቶች አጠቃቀሙ የሚያበረታታ ነው። ክርስቲያኑ ከዚህ የሚማራቸው በርካታ ቁም ነገሮች አሉ።

ከሙስሊም እንቅስቃሴና ወያኔ ይህንን እንቅስቃሴ ለማፈን እየሰዳቸው ካሉ እርምጃዎች የምንረዳው አንድ ትልቅ ሐቅ የቱን ያህል ጨዋና የሰለጠነ ቢሆን ወያኔ የሕዝብ ድምጽ ለማዳመጥ ፍላጎት የሌለው መሆኑን ነው። ሙስሊም ወገኖቻችን ጥያቄዎቻቸውን በሚያስገርም ቁጥብ ሥነሥርዓት (ዲሲፒሊን) ቢያቀርቡም ከወያኔ የተሰጠው ምላሽ ግን አፈና፣ ረገጣ፣ ቶርቸር እና ከእስከዛሬዎቹ ይበልጥ አፋኝ የሆኑ ደንቦችና ድንጋጌዎችን ነው። ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ያደረጓቸው ትግሎችም እንደዚሁ ወደ ባሱ የመብት ጥሰቶች እያመሩ ነው። ከዚህ የምንማረው ነገር ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ስትራቴጂዎችን መፈተሽ እንደሚያስፈልግ ነው።

እንደሚታወቀው፤ ሰብዓዊ መብቶች እርስ በርሳቸው የተቆራኙ፤ እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ ናቸው። አንዱ የመብት ዓይነት ሲጓደል፤ ሌላውም አብሮ ይጓደላል። ለምሳሌ የመናገር መብት ተገፎ እያለ የማምለክ መብት ሊፋፋ አይችልም፤ ወይም ደግሞ ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ተጥሶ እያለ የማምለክ መብትን የሚያስከብር ተቋም ሊኖር አይችልም።

ለመብቶች መከበር የሚደረጉ ትግሎች፤ በተለይም ደግሞ የሙስሊም ወገኖቻችን ትግል የደረሰበት ደረጃ በአንክሮ ሲጤን ስትራቴጂን በተመለከተ በጥልቀት ልናስብባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን እንገነዘባለን። ለጊዜው ሁለት ነገሮች ላይ አጽንዖት ሰጥተን እናልፋለን።

1. ከላይ እንደተገለፀው የመብት ትግሎች ሁሉ መደጋገፍ ይኖርባቸዋል። ቀደም ሲል በባህርዳር፣ በኋላም በአዲስ አበባ በሴቶች ዓለም ዓቀፍ ቀን አሁን ደግሞ በደሴ ውስጥ እንደታየው የመብት ጥያቄዎች ሁሉ ተደጋግፈው መነሳት ይኖርባቸዋል። ይህ የመደጋገፍ ልምድ የሁለቱ ትላልቅ ሃይማኖቶች ተከታዮች ለየእምነቶቻቸው ነፃነት በሚያደርጉት ትግል ውስጥ መኖር ይኖርበታል። የሙስሊሞች የመብት ጥያቄዎች የክርስቲያኖችም፤ የክርስቲያኖች ደግሞ የሙስሊሞችም መሆን ይኖርበታል።
2. በሥልጣን ላይ ያለው የህወሓት አገዛዝ አንዱንም የመብት ጥያቄ መመለስ የማይችል መሆኑ ግልጽ መሆን ይኖርበታል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የመብት ጥያቄዎች ግብ ወያኔን ከሥልጣን ከማባረር ያነሰ መሆን አይችሉም። ስለሆነም የመብት ማስከበር ትግል ስናካሂድ ይህን አልመን እና ለዚህም ተዘጋጅተን መሆን ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ የስነልቦና፣ የድርጅትና የስልት ዝግጅት ይጠይቃል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ህወሓት ከሥልጣን መወገድ ይኖርበታል ብሎ ያምናል። ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ መገለል፣ መረገጥ፣ መጋዝ፣ መሰደድ፣ መደብደብ፣ የማይቀርልን በመሆኑ ሥቃያችንን ለመቀነስ ወያኔን ማስወገድ ይኖርብናል ብሎ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ መንገዶችና ምክንያቶች የምናደርጋቸው ትግሎች ወደ አንድ አቅጣጫ ያመራሉ ብሎ ያምናል። ትግሎቻችን ዞሮ ዞሮ ህወሓትን ከሥልጣን ወደ ማስወገድ ማምራታቸው ግልጽ ስለሆነ ለዚህ የሚያስፈልገውን ስነልቦናዊና ቁሳዊ ዝግጅቶችን እናድርግ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

### ኢትዮጵያ ዉስጥ የሰብአዊ መብት አያያዝ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ምስክርነቱን ያደመጡና የምስልና የጽሁፍ ማስረጃዎችን የተመለከቱ አንዳንድ የፓርላማው አባላት እነዚህ ማስረጃዎች በኢትዮጵያው አገዛዝ ላይ ከፍተኛ ማእቀብ ለመጣል ከበቂ በላይ ስለሆኑ የኢኮኖሚ ማእቀብ መጣል ይገባናል ሲሉ የተደመጡ ሲሆን የአውሮፓ ሕብረት ፓርላማ ከፍተኛ አመራሮችና ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው የፓርላማው አባላት ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእርዳታ ገንዘብ አሰጣጥንና አጠቃቀሙን በተመለከተ በሕወሃት መራሹ ወያኔ ላይ አሳሪ ህግ ያጸድቃሉ ተብሎ ይጠበቃል። የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የቀድሞ ከፍተኛ አማካሪና አሁን በስደት የሚገኙት አብዱላሂ ሁሴን እንዲሁም በስዊድን ጋዜጠኛና በኢትዮጵያ ከአንድ ዓመት በላይ በእስር ላይ የነበረው ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብዬ ለፓርላማው ምስክርነታቸውን የሰጡ መሆኑ ተያይዞ ተገልጿል።

### የ2007ቱ ምርጫ በተቃረበ ቁጥር የወያኔ አፈና፤

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መጋዛቸው ቀጥሏል በማለት የህወሃትን አፈና ያማራራሉ።

በአዲስ አበባ የሰማያዊና የአንድነት ፓርቲ አባላት እስር ቤት ገብተው እንደነበር የተጠቆመ ሲሆን በትግራይ ደግሞ የእረና ፓርቲ ሰዎች በተደጋጋሚ እስርቤት እንዲገቡ ተደርጓል ተብሏል። ይሁን እንጅ ይህን ሁሉ አፈናና እስራት በመጋፈጥ አረና በትግራይ አንድነት ፓርቲ ደግሞ በደሴ የሚሊዮኖች ድምጽ ለመሬት ባለቤትነት በሚል መርህ ውጤታማ የነበረ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸው ተሰምቷል።

## ደሴዎች ሆይ !

## ቁጭታችሁ ቁጭታችን፤ ብሶታችሁ ብሶታችን ነው።

በደሴ ሚሊየኖች የመሬት ባለቤት እንሁን ሲሉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ጮኸዋል።መሬት ክብር ነው። መሬት ሃብት ነው። መሬት ማንነትም ነው።ይህ ክብር፤ ይህ ሃብት፤ ይህ ማንነት ከህዝቡ ላይ ተወስዷል። በኢትዮጵያ ውስጥ የመሬቱ ባለቤት ህወሃት-ኢሕአዴግ ነው። ይሄ ቡድን መሬቱን ብቻ ሳይሆን ህዝቡንም "የእኔ ንብረት ነው" የሚል አስተሳሰብ አሳድሯል። በዚህ አስተሳሰቡም የወደደውን ሲተክል፤ የጠላውን ሲነቅል ብዙ ዓመት ኑሯል። ከዝያም "ህዝቡ ተኛ ብንለው ይተኛል፤ ተነስ ስንለውም ይነሳል" እያለም ይሳለቃል። እውነት ነው መሬት አልባ የሆነ ዜጋ ተኛ ሲባል ከመተኛት፤ ተነስ ሲባልም ከመነሳት ሌላ ምን የተሻለ አማራጭ አለው? ለዚህ አማራጭ ላጣ ህዝብ አማራጭ ይኖረው ዘንድ የምትተጉ ወገኖችን ከልብ እናደንቃለን።

የደሴውን ሰልፍ ያዘጋጃችሁ ዜጎች ተስፋ አለመቁረጣችሁ ይደነቃል። ከፍ አድርጋችሁ የጮኻችሁት ጩኸት በኢትዮጵያ ውስጥ ከዳር አሰከ ዳር ተስተጋብቷል። ይሄን ድምፅ ያልሰማው ህወሃት-ኢሕአዴግ ብቻ ነው። ይሄ ቡድን "ማን አባቱ ይጠይቀኛል" የሚል ከንቱ እብሪት ዓይኖቹ እንዳያዩ፤ ጆሮዎቹም እንዳይሰሙ ስላገዱት የሰልፉን ድምፅ አላየሁምም አልሰማሁምም ብሏል። ህወሃት ማስተዋል የሚችል ቢሆን ኑሮ ይሄን ድምፅ አድምጦ መልስ ቢሰጥ እንደሚበጀው ያውቅ ነበር። ግን ምን ያደርጋል "እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይበቀል" የምትለዋን እንስሳ መምሰልን የመረጠ ቡድን በመሆኑ ይሄን መሰሉን ድምፅ ሲሰማ "እኔ የኢያሪኮ ግንብ አይደለሁም በጩኸት የምናደው " እያለ ይሳለቃል።እንዲያውም "የእኔን ፖሊስ ማስቀየር የሚቻለው በመቃብሬ ላይ ነው" እያለ እንደሚፎክርም መታወቅ አለበት።

ህወሃት-ኢሕአዴግ መንግስት ሊሸከመው የሚገባውን አገራዊ ኃላፊነት ለመሸከም ብቃት ያለው ቡድን አይደለም። ይሄ ቡድን የመንግስት ቅርፅና መልክ የለውም። የዚህ ቡድን መልኩና ቅርፁ "የመርሲነሪስ" መልክና ቅርፅ ነው። ይህን መልክና ቅርፅ የያዘን ቡድን ነጭ ሪባን እያውለበለብኩ ከያዘው የጥፋት ጎዳና እመልሰዋለሁ ብሎ ማመን ለእኛ የሚቻል አይደለም። የማይቻለውን ይቻላል ብላችሁ የተነሳችሁ ወገኖች ትዕግስታችሁን እናደንቃለን። ህወሃት ከሆነው ወይም ከተናገረው ውጪ ሌላ ስብዕና የለውም። የያዝኩት የጥፋት መንገድ የሚቀየረው በመቃብሬ ላይ ነው፤ ፖሊሲየን ለማስቀየር የሚፈልግ ካለም በሊማሊሞ በኩል ብቅ ይበል ማለቱ እውነት ነው። እኛ ይሄን እውነት አምነናል። የእናንተን ትጋትና ት ዕግስት ግን ከልብ እናደንቃለን።

ሠላማዊ ሠልፍ ማድረግ የዜጎች የማይገሰሰ መብት ነበር። ህወሃቶች ፅፈው ለህዝቡ የሰጡት ህግ መንግስትም ይሄን ይመስከራል። ሠላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ማሳወቅ እንጂ ፈቃድ መጠየቅ አያሰፈልግም የሚል ህግም አለ። ህወሃት-ኢሕአዴጎች ግን በዚህ ቀን አልፈቀድንም፤ በዚህ አካባቢ ከልክለናል እያሉ ራሳቸው የሠሩትን ህግ ከአፈር ይቀላቅሉታል። በዚህም የዜጎችን የመሰብሰብ መብት ይጥሳሉ። ጣሊያኖች በአገራችን በቆዩባት በዚያች አጭር ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያዊያንን በዚህ በኩል አትለፉ፤ በዚያ በታች በኩል ሂዱ እያሉ ያንገላቱ ነበር። ህወሃት-ኢሕአዴጎችም ቀኝ ገዢዎች የሚፈፅሙትን ዓይነት አድሎ በዜጎች ላይ እየፈፀሙ ይገኛሉ። ኢትዮጵያዊያን በመስቀል አደባባይ መሰበስብ ሲከለከሉ፤ ህወሃት-ኢሕአዴጋዊያን ግን በመስቀል አደባባይ ከበሯቸውን እየደለቁ በደስታ ይጨፍሩበታል ማንስ ይከለክለናል እያሉ ያዜሙበታል።

እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን ክፉና ዘረኛ ቡድንን በሰላም አደብ ለማስገዛት የምትጥሩ ወገኖች በርቱ።ባለፈው በባህር ዳር የተደረገው የተቃውሞ ሠልፍ በግሩም ሁኔታ ተጠናቋል። ከባዶ ጭንቅላት ባዶ እግር እንደሚሻልም አስተምሯል። ከሠልፉ በኋላ መንግስት ነኝ ከሚለው አካል የተሰጠ መልስ የለም።ዓለምነህ መኮንን ግን እስከ አሁን በወንበሩ ላይ አለ። አሁን ደግሞ በደሴ " የሚሊየኖች ድምፅ ለመሬት ባለቤትነት" በሚል መሪ ቃል ሠልፍ ተደርጓል። ይሄም በግሩም ሁኔታ ተጠናቋል። አሁንም መልስ የሚሰጥ አካል ብቅ አለማለት ብቻ ሳይሆን ሠልፉን የሰማም አይመስልም። ነገ ደግሞ በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢ ሌላ ሰልፍ ይደረጋል። ይሄም ግሩም ሃሳብ ነው።ከሰልፉ በኋላ የህዝቡን ሮሮ ሰምቶ መልስ የሚሰጥ አካል ይኖር እንደሆነ አብረን እናያለን።

ኢትዮጵያዊያን መከራችን ቡዙ ነው።ዋነኛው የመከራችን ምንጭ ግን ህወሃት-ኢሕአዴግ ነው። በአሁን ሠዓት በኢትዮጵያችን ከተጋረጠው ችጋር በላይ ችግር የሚሆንብን ህወሃት ነው። ይሄ ዘረኛ ቡድን የመከላከያ ኃይሉን፤ የደህንነት ተቋሙን፤ የንግድ አምባዎችን ያቆመበት መሠረት ከሶሪያው አሳድ አገዛዝ ጋር አንድ ነው። ዛሬ ሶሪያ የገባችበት መከራ በቀላሉ የሚቋጭ አልሆነም። ምክንያቱም የስልጣኑን እርከን የተቆጣጠሩት ቡድኖች መሠረታቸውን ያቆሙት በጎሳ ላይ በመሆኑ ነው። የህወሃት መሠረቱ ጎሳ ነው። በጎሳ ተደራጅቶ የሌላውን ጎሳ ሲያንገላታ እነሆ ሁለት አሥርተ ዓመታት ሞላው። በጎሳ ተደራጅቶ ሌላውን ሲዘርፍ ብዙ ዓመት ተቆጠረ። ሌላው ጦሙን ሲያድር እርሱ ብቻ በልቶ የሚያድር ሆነ። የሌላው ልጅ በበርሃ ቀልጦ ሲቀር፤ ገሚሱ የአዞ እራት ሲሆን የእርሱ ልጆች ግን በአውሮፓና በአሜሪካን ለትምህርት የሚላኩ ሆኑ። በህወሃት የሚፈፀመውን አድልዎ በቃል ለመግለፅ ከምንችለው በላይ ነው። እንዲህ መሠረቱን በአድልዎና በጎሳ ላይ ያቆመ ቡድንን ከተቆናጠጠበት የዝሪፊያ ወንበር ላይ ለማውረድ የሚጠይቀው መሥዋዕትነት በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። እስከ አሁንም ብዙ መሥዋዕትነት ተከፍሏል። ገና ወደፊትም ብዙ መሥዋዕትነት ይጠይቃል። ለዚህ ራስን በቅጡ አደራጅቶና ተባብሮ መታገል ግዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ሁኗል።

የመንግስት ሳይሆን የወሮ በላ መልክና ቅርፅ ካለው ቡድን ፊለፊት ቆማችሁ በየቦታው የምታሰሙት የተቃውሞ ድምፅ መልካም ነው።ብዙ መሥዋዕትነትም እያሰከፈላችሁ እንደሆነ እንገነዘባለን። ይሄ የምትከፍሉት መሥዋዕትነት በከንቱ እንዳይሆን ግን አጥብቆ ማሰብ ይገባል። እስከ አሁን ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዋል። የአማራን ህዝብ ያዋረደው ግለሰብ ለፍርድ ይቅረብ የሚል ድምፅ በባህር ዳር ተስተጋብቷል። የአማራን ህዝብ የሰደበው ግለሰብ ግን እኔ አልተሳደብኩም፤ ተቃዋሚዎች ቆርጠው ቀጥለው ያቀረቡት ነው እያለ ይሳለቃል። በሌላ በኩል ደግሞ በከተማዋ ውስጥ ያሉትን ኮምፒውተሮች ለቃቅሞ መረጃውን የላከውን ዜጋ ፍለጋ ሌሎች ዜጎችን እያሰቃየ ይገኛል። ይህን መሰሉን ንቀት ልንሸከም አይገባንም። ህወሃት-ኢሕ አዴጎች ለህዝብ ጥያቄ መልስ እንዳይሰጡ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ እንደገና መጠየቅ ይኖርበታል። የሚመራውን ህዝብ የሰደበ ግለሰብ ለፍርድ መቅረቡ አግባብ ነው። ይሄ ስደብ ግን የግለሰብ አፍ ወለምታ ሳይሆን የድርጅቱ አቋም ነው። ድርጅቱ ለፍርድ ሊቀርብ አይችልም። አዎን ኢሕኢደግ አይከሰሰም፤ ሰማይም አይታረስም የሚል ተረት አላቸው። እንግዲህ ምን ይሻላል? ይሄ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን ትክክለኛውን መልስ እስኪሰጥ ድረስ ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ትክክለኛዋ መልስ ደግሞ ሰዳቢው ለፍርድ መቅረብ ብቻ ሳይሆን ፍትህ፤ እኩልነት እና ነፃነት በዚያች አገር ነግሰው መታየት ነው።

የተከበራችሁ ያገራችን ዜጎች አገራችን ያለችበት ችግር ከእሪታ በላይ ነው። እሪ ብንልም የሚሰማ መንግስት የለንም። የሚሰማ መንግስት የለም ተብሎ ዝም ማለት ግን ትክክለኛ ምርጫ አይደለም። በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጫንቃችን ላይ ቁጢጢ ያሉ ወሮበላዎችን ማስወገድ ግድ ነው። ህወሃት-ኢህአዴጎች ሳይፈለጉ በዜጎች ጫንቃ ላይ ቁጢጢ ብለው ሃያ ዓመት አለፋቸው። "ሳንፈልጋቸው ሃያ ዓመታቸው" የሚባል ቅኔ ቢዘረፍላቸውም አልገባቸውም። የእነርሱ ምኞት ሌላውን ሁሉ እንደ ሰም አቅልጦ፤ እንደብረት ቀጥቅጦ መግዛት ነው። ሁል ግዜ እነርሱ ከላይ፤ ሌላው ሁሉ ከታች እነርሱን ተሸክሞ እንዲኖር ብርቱ ምኞት አላቸው። ይሄንንም እውን ለማድረግ ራሳቸውን ህግ አድርገው ቀርፀዋል። የአገሪቷም ፍትህ በእነርሱ ስሜት እየተወሰነ ዜጎችን ለማጥቂያነት ውሏል። የፍትሁን ሥርዓት አፈር ከድሜ ካስገቡት በኋላ ሰለዴሞክራሲ ሊነግሩን ሲነሱ የዓይናቸው ሽፋሽፍት እንኳ አይርገበገብም። እነዚህ ቡድኖች ጭካኔን ከጀግንነት መለየት የማይችሉ ፍፁም ርህራሄ የሌላቸው ናቸው። ይሄን ቡድን ነጭ ሪባን እያውለበለቡ ከተቆናጠጡበት ወንበር የማውረዱ ትግል ቢሳካ ለሁላችንም እፎይታ ይሆን ነበር።እኛ ግን ህወሃት-ኢሕአዴግ በሠላማዊ መንገድ ስልጣኑን ለህዝብ ያስረክባል የሚል እምነት የለንም።

### የተከበራችሁ ወገኖቻችን!

እንግዲህ እናንተም በያዛችሁት መንገድ እንዲሳካላችሁ እንመኛለን። እኛም በአገራችን ፍትህ፤ እኩልነት እና ሙሉ ነፃነት እስከሚሰፍን ድረስ የጀመርነውን ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን። የእኛም ሆነ የእናንተ መዳረሻ ግቡ አንድና አንድ ነው። አገራችን ከዘረኞችና ከዘራፊዎች ፀድታ፤ ፍትህ እኩልነትና ነፃነት ነግሶ፤ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶ እና ሠላም ሠፍኖ ማየት ነው ግባችን።እኛ በሊማሊሞ በኩል ብቅ በሉ ያሉትን ሰምተን በዚያው አያቶቻችን ባለፉበት የነፃነት መንገድ ልንጓዝ ስንቃችንን እያሰናዳን ነው። የአያቶቻችንን ጋሻና ጦር ከተሰቀለበት አውርደን እየወለወልን ነው። ከእንግዲህ ወዲያ ከህወሃት-ኢሕአዴግ የምንጠብቀው ምንም በጎ ነገር የለም። እነርሱ ተጭነውን፤ እኛ ተሸክመናቸው ለዘላለም አንኖርም። እነርሱ ሰጪ እኛ ተቀባይ፤ እነርሱ ፈቃድ ሰጪ እነርሱ ፈቃድ ከልካይ ሆነን ለዘላለም አንኖርም። ለነፃነት የሚከፈለውን ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ሳናቅማማ ተነስተናል።

በመጨረሻም ለህወሃቶች እንዲህ እንላችኋለን "ነፃነታችንን ስጡን ወይም ነፍሳችንን እንኳት" አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የወያኔ ፖሊሶች ከ20 በላይ የቦዲ ብሄረሰብ ተወላጆችን መግደላቸዉ ተሰማ

ነብሰ ገዳዮቹ የወያኔ ጸጥታ ኃይሎች በቅርቡ በቦዲና በኮንሶ ብሄረሰቦች መካከል የተከሰተዉን ግጭት እናበርዳለን በሚል ሰበብ በወሰዱት የማጥቃት እርምጃ ከሃያ በላይ የቦዲ ብሄረሰብ ተወላጆችን ሳይገድሉ እንደልቀረ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኝ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አስታወቀ። የኦሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ህብረት ምክትል ሊቀመንበርና የዞኑ ሰብሳቢ አቶ አለማየሁ መኮንን ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ባለፈው አንድ ወር ውስጥ በቦዴዎችና በኮንሶች መካከል የተነሳውን ግጭት ተከትሎ የፌደራል ልዩ ሃይል በወሰደው እርምጃ ወደ 29 የሚጠጉ ሰዎች መገደላቸውን ነዋሪዎች ለድርጅታቸው ሪፖርት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የሟቾችን ስም ዝርዝር በማጠናቀር ላይ ሲሆኑ ሰሞኑን ይፋ እንደሚያደርጉም ምክትል ሊቀመንበሩ ተናግረዋል ሆስፒታል ሄደው የቆሰሉትን ሰዎች መጎብኘታቸውና ማነጋገራቸውን የሚናገሩት አቶ አለማየሁ ፣ ከሁለቱ በስተቀር ሌሎች ወደ 6 የሚጠጉ ሰዎች በፌደራል ፖሊስ ጥይት መቁሰላቸውን እንደገለጹላቸው ተናግረዋል።

ምንም እንኳ የግጭቱ መነሻ መንግስት ካሰፈራቸው የኮንሶ ተወላጆች ጋር የተያያዘ ቢመስልም፣ ቦዴዎች ለሸንኮራ ገዳ ተክል በሚል ከአካባቢያቸውን እንዲነሱ መደረጉ የፈጠረባቸው ስሜት የችግሩ ዋነኛ መነሻ መሆኑን ገልጸዋል። ቦዴዎች ዘላኖች በመሆናቸው ለዛፎች ልዩ እንክብካቤ እንደሚያደርጉ የገለጹት ባለስልጣኑ፣ በእርሻ ስራ የሚተዳደሩት ሰፋሪ ኮንሶዎች ወደ አካባቢያቸው በመግባት ዛፎችን እየቆረጡ የእርሻ ማሳ ሲያስፋፉ ሲመለከቱና ለሸንኮራ ልማት በሚል ቀያቸውን እንዲለቁ ሲገደዱ የፈጠረባቸው ቁጭት ደም አፋሳሽ ወደ ሆነ ግችት ተቀይሯል።ምንም እንኳ በሁለቱ ጎሳዎች መካከል የተነሳው ግጭት በፌደራል ፖሊስ የሃይል እርምጃ ቢቆምም፣ ውጥረቱ እንዳለ መሆኑን አቶ አለማየሁ ገልጸዋል። እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የፌደራል ፖሊስ አሁንም ድረስ በአካባቢው ይገኛል።

## የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የኮካ ኮላ ምርት ክልሌን አይረጥም አሉ

የሶማሌ ክልል ፕሬሲዳንት የሆኑት አብዲ ሙሃመድ የኮካ ኮላ ምርት ሶማሌ ክልል ዉስጥ በክልሉ ተወላጅ በሆኑት በወይዘሮ ሀዋ የማይከፋፈል ከሆነ ኮካ ኮላ ወደ ክልሉ እንዳይገባ አደርጋለሁ አሉ። ይህንን ተከትሎ የወያኔ ቤተሰቦች በሆኑ የኮካ ኮላ አከፋፋዮችና በፕሬዚዳንቱ መካከለል በተነሳዉ አለመግባባት የተነሳ ባለፉት 2 ሳምንታት የኮካ ኮላ ምርት ወደ ክልሉ እንዳይገባ በመታገዱ የሶማሌ ልክልል ነዋሪዎች ከሶማሊላንድ እየታሸገ በኮንትሮባንድ የሚገባውን ኮካ ኮላ ለመጠቀም ተገድደዋል። ይህ የሁለትዮሽ ጭቅጭቅ ኢትዮጵያ በሚገኘው በኮካ ኮላ ድርጅትና በክልሉ መንግስት መካከል ልዩነት መፈጠሩም ታውቋል።ቀደም ብሎ በክልሉ የኮካ ምርትን የሚያከፋፍለው የታዋቂዋ ባለሃብት የወ/ሮ ሱራ ድርጅት ሲሆን፣ የክልሉ ፕሬዚዳንት አብዲ ሙሃመድ ግለሰቡዋ የኦጋዴን ተወላጅ ባለመሆናቸው ለወ/ሮ ሃዋ እንዲሰጥ በመወሰናቸው ነው።ወ/ሮ ሃዋ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በክልሉ ቁጥር አንድ ባለሃብት እየሆነች የመጣች  ዮሃንስ ገብረመስቀል የፍቅር ጓደኛ ናት።

ወ/ሮ ሱራ ከ ወ/ሮ አዜብ መስፍን ጋር በሽርክና በመስራት ጫት ከኢትዮጵያ ወደ ሶማሊላንድ በማመላለስ ከፍተኛ ሃብት አካብታለች። ግለሰቡዋ ሶማሊላንድ ላይ ግንባታዎችን ማካሄዱዋን እንደሰበብ የተጠቀሙበት የክልሉ ፕሬዚዳንት፣ ኮካን የማከፋፈሉን ስራ ከወ/ሮ አዜብ የንግድ ሸሪክ ወደ ጄኔራል ዮሃንስ ገብረመስቀል የፍቅር ጓደኛ አዞረዋል።መስተዳድሩ የኮካን ምርት ወ/ሮ ሃዋ የማታከፋፍል ከሆነ ኮካ ኮላ በክልሉ መሰራጨት የለበትም የሚል አቋም መያዙን ተከትሎ፣ የኮካ ኮላ መስሪያ ቤት ለሁለቱም ባለሀብቶች መስጠቱን ትቶ ራሱ ማከፋፈል እንደሚጀምር መግለጹ ታውቋል።

በክልሉ መሪ በአቶ አብዲና በወ/ሮ አዜብ መስፍን መካከል የተፈጠረው ልዩነት ወ/ሮ ሱራ የኮካ ኮላ ማከፋፈሉን ስራ እንድትነጠቅ ከማድረጉም በላይ ወደ ሶማሊላንድ ስትልከው የነበረውንም ጫት ከወ/ሮ ሃዋ ጋር በየሁለት ሳምንቱ ተካፍለው እንዲልኩ በመወሰናቸው ወ/ሮ ሱራን ከጫዋታ ውጭ እያደረጉዋቸው ነው።ወ/ሮ ሃዋ በጅጅጋ፣ በደገሃቡርና በመቀሌ የተለያዩ ግንባታዎችን እያካሄዱ ነው። ጄ/ል ዮሃንስ በክልሉ ውስጥ በአዛዥነት ይሰሩ በነበረበት ወቅት የተለያዩ የመከላከያ ኮንትራቶችን ለወ/ሮ ሃዋ በመስጠት በአንድ ጊዜ ከኢንቨስተሮች ተራ እንድትገባ አድርገዋታል።

ወ/ሮ ሱራ በበኩላቸው ከጠ/ሚንስትር መለስ ሞት በሁዋላ በክልሉ ያላቸው ተሰሚነት እየቀዘቀዘ በመምጣቱ ትኩረታቸውን ሁሉ ሶማሊላንድ ላይ ለማድረግ ተገደዋል።በጣም የሚገርመው ይላል ምንጫችን ኮካ ኮላ በህጋዊ መንገድ እንዳይገባ ከተደረገ በሁዋላ በኮንትሮባንድ ከሶማሊላንድ እያስገቡ የሚሸጡት ጅጅጋን የሚያስተዳድሩት የህወሀት የመከላከያ አዛገኖች ናቸው። እነዚህ አዛገኖች ያለምንም ከልካይ ኮካ ኮላ በማምጣትና በማራገፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ እያጋበሱ ነው።

ጄ/ል ዮሃንስ ጄ/ል ሳሞራ የኑስን ይተካሉ ተብሎ ይጠበቃል። በአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለከተማ ከ70 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ ዘመናዊ የንግድ ድርጅት መገንባታቸውን ኢሳት በፎቶ ግራፍ አስደግፎ ማቅረቡ ይታወቃል።የህወሃት የመከላከያ አዛገኖች ጅጅጋን የሃብት ማግኛ ማእከላቸው አድርገው እንደሚቆጥሯት የክልሉ ተወላጆች ሲገልጹ ይሰማል።በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ የክልሉ የገጠር ከተሞች በአንበጣ መንጋ መወረራቸው ታውቋል። የክልሉ መንግስት እስካሁን ምንም አይነት እርምጃ አለመውሰዱንም የደረሰን መረጃ ይገልጻል።

## አወዛጋቢዉ  የመረጃና ደህንነት አገልግሎት አዋጅ ሥራ ላይ ዋለ

ባለፈው ዓመት መጨረሻ በአዲስ መልክ በአዋጅ የተቋቋመውና ዜጎች መረጃ እንዲሰጡ የሚያስገደድደው ብሔራዊ የመረጃ ደህንነት አገልግሎት አዲሱን አዋጅ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን ምንጮች ገልጸዋል።

በ1987 ዓ.ም የደህንነት የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን በሚል ስያሜ ተቋቁሞ በስራ ላይ የነበረው ይህው ተቋም የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት እንዲችል በሚል ባለፈው ዓመት አዲስ የማሻሻያ ረቂቅ ለፓርላማው ቀርቦ መጽደቁ ይታወሳል።

አዲሱ አዋጅ ካስፈለገባቸው ምክንያቶች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በመረጃና ደህንነት ዙሪያ የስጋቶች ምንጭ እና የመከላከያ ስርዓትና አሰራር እየተለዋወጠ በመምጣቱ፣በአገር ውስጥ የጸረ ሽብርተኝነት እና የበረራ ደህንነት የማስጠበቅ የመረጃና ደህንነት ተጨማሪ ሃላፊነቶች በአገልግሎቱ ስልጣንና ሃላፊነት ውስጥ እንዲካተቱ እንደተደረገ ያገኘነው መረጃ ይጠቅሳል።

በዚህ አዋጅ መሠረት በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ ሌላ የመረጃና ደህንነት መ/ቤት ማቋቋም የተከለከለ ሲሆን የመ/ቤቱ ገቢና ወጪ ሂሳብ ይፋዊ በሆነ መንገድ በኦዲተር እንዳይመረመርና ሂሳብ ነክ ጉዳዮች ለጠ/ሚኒስትሩ ብቻ ሪፖርት እንደሚያደርግ ደንግጓል። ለመ/ቤቱ ከውጪ ተገዝተው የሚገቡና በተለያየ ምክንያት ለስራ ተብለው የሚወጡ ዕቃዎች ጉምሩክ ሳያያቸው እንዲወጡና እንዲገቡ የተደነገገ ሲሆን የደህንነት ሠራተኞች ሃብት ምዝገባ በጸረ ሙስና ኮምሽን ሳይሆን በተቋሙ እንደሚከናወን ይገልጻል።

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በተጨማሪም ግለሰቦችም ሆኑ ተቋማት መረጃ በሚጠየቁበት ጊዜ ትብብር ያለማድረግ ሁኔታ ለሥራው እንቅፋት መሆኑን በመጥቀስ መረጃ መስጠት ግዴታ እንዲሆን በአዋጁ ደንግጓል። ይህን አዋጅ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ለማዋል ተቋሙ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንና በተለይ ከመጪው ዓመት አገር አቀፍ ምርጫ ጋር ተያይዞ ሕግና ስርዓትን ለማስከበር በሚል ዜጎች መረጃ ስጡ እየተባሉ ለእንግልትና ለእስር እንዳይዳረጉ ከወዲሁ ስጋት ፈጥሮአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዲያስፖራዉ ለወገኖቹ የሚልከዉ ገንዘብ የኢትዮጵያ ቀዳሚ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ መሆኑ ታወቀ

ኢትዮጵያ በ2005 በጀት ዓመት ምረቶቿን ለዉጭ ገበያ ልካ ካገኘችዉ ገቢ ይበልጥ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ለወገኖቻቸዉ ከሚልኩት ገንዘብ ያገኘችው ገቢ እንደሚበልጥ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ የጹሑፍ መረጃ አመልክቷል። ይህ አክራሪ ወይን አገሩን የከዳ ዳያስፖራ እየተባለ በወያኔና በደጋፊዎቹ የሚጠላዉ ዳያስፖራ በብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዝብ ወደ አገሩ በመላክ የዳያስፖራዉ ችግር የወያኔ ዘረኝነት ነዉ እንጂ አገሩና ወገኑ አለመሆኑን በተግባር አሳይቷል ሲሉ አንድ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪ ተናግረዋል።

ከወያኔ ባለስልጣኖች የተገኘዉ መረጃ እንደሚያሳየው በ2005 በጀት ዓመት አገሪቱ ከኤክስፖርት 3.1 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ያገኘች ሲሆን ኢትዮጵያውያን ከውጭ ከሚልኩት ገንዘብ ደግሞ 3 ቢሊዮን 9 መቶ ሚሊዮን ዶላር አግኝታለች። በ2004 በጀት ዓመትም ከሐዋላ እና ከኤክስፖርት ያገኘችው ገቢ ተመሳሳይ ማለትም እያንዳንዳቸው 3.2 ቢሊየን ዶላር መሆኑን መረጃው ያሳያል።መረጃው የሐዋላ ገንዘብ በፍጥነት እያደገ ሲመጣ በአንጻሩ አገሪቱ እንደቡና ፤የቅባት እህሎችና ጥራጥሬና የመሣሠሉትን በመላክ የምታገኘው ዓመታዊ ገቢ እያሽቆለቆለ መምጣቱን ያሳያል።

የኤክስፖርት ዘርፍ ባለፉት ሶስት ዓመታት መንግስት ከያዘው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙ ደካማ መሆኑን መረጃው የሚጠቁም ሲሆን ከገቢ ንግድ ጋር ያለው የንግድ ሚዛን ጉድለት እየሰፋ መምጣቱ አሳሳቢ መሆኑን ያመለክታል።በ2004 የገቢ ንግድ(ኢምፖርት) መጠን 11 ቢሊየን ዶላር ሲሆን በ2005 ዓ.ም ወደ 11. ቢሊዮን 500 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ብሎአል። የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ከሸቀጦች የገቢ ንግድ ወጪ ጋር ሲነጻጸር በሚጠበቀው ደረጃ ዕድገት ባላማሳየቱ የንግድ ሚዛን ጉድለቱ በ2003 ዓ.ም ከነበረበት 5 ቢሊዮን 500 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በ2005 ዓ.ም ወደ 8. ቢሊየን 400 ሚሊዮን ዶላር እንዲሰፋ ማድረጉን መረጃው ጠቁሟል። ይህን የንግድ ሚዛን ጉድለት ለማጥበብ መፍትሔው ኤክስፖርትን ማሳደግ ነውም ብሏል።እጅግ የተለጠጠ ነው በሚል ትችት የሚቀርብበት የመንግስት የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት ታሳቢ ከተደረገው ገንዘብ መካከል ብድርና እርዳታ አንዱ መሆኑ ይታወቃል። መረጃው እንደሚያሳየው ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ለጋሽ መንግስታት አገሪቱ ያገኘችው ዕርዳታ በ2005 ዓ.ም ማሽቆልቆል አሳይቷል።

## ወ/ሮ አስቴር ማሞን ሹመት አገኙ

ወያኔ መልምሎ ያቀረበለትን የደካማ ግለሰቦች ሹመት ፓርላማ እየወሰደ አጽድቁልኝ ከማለት ሌላ ይህ ነዉ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ስልጣን የሌላዉ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ በያዝነዉ ሳምንት ማብቂያ አካባቢ የኦህዴድ ምክትል ሊቀመንበርና የጽ/ቤት ኃላፊ የነበረችዉን ወ/ሮ አስቴር ማሞን በምክትል ጠ/ሚኒስትር ማዕረግ የመልካም አስተዳደር ክላስተር አስተባባሪና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር እንድትሆን ያቀረበዉን ሹመት ፓርላማው ተቀብሎ አጽድቋል።

የኦህዴድ ሊቀመንበርና የክልሉ ፕሬዚደንት ከነበሩት አቶ አለማየሁ አቶምሳ ሞት በኃላ ኦህዴድ ባደረገው የሥልጣን ሽግሽግ አቶ ሙክታር ከድር ከምክትል ጠ/ሚኒስትርነት ተነስቶ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚደንት ሆኖ መሾሙ የሚታወስ ሲሆን ወ/ሮ አስቴር ማሞ ደግሞ በአቶ ሙክታር እግር ተተክታለች።

ወ/ሮ አስቴር ማሞ በጳጉሜ ወር 2002 ዓ.ም በተካሄደው የኦህዴድ ጉባዔ ከድርጅቱ ሥራ አስፈጻ ኮምቴ አባልነት አሰናብቷት የነበረ ሲሆን በመጋቢት ወር 2005 ዓ.ም የተካሄደው የኦህዴድ ጉባዔ አባዱላ ገመዳን፣ ኩማ ደመቅሳንና፣ግርማ ብሩን ከፓርቲው ሥራ አስፈጻሚነት ሲያሰናብት የወያኔ ታማኝ ሎሌ መሆኗ የሚነገርላት ወ/ሮ አስቴር እንደገና መመረጧ የሚዘነጋ አይደለም። የአቶ አለማየሁ አቶምሳን ሞት ተከትሎ በቅርቡ ፓርቲው ባደረገው ሽግሽግ አስቴር ማሞ ከኦህዴድ ጽ/ቤት ኃላፊነቷ በተጨማሪ የፓርቲው ምክትል ፕሬዚደንት ሆና ተሹማለች።